# ስለ ክንፈረንሱ

በመጋቢት 2010፣ የነዶክተር  ዐቢይ ቡድን፣ ኢህአደግ ውስጥ በተፈጠረው የለውጥ እንቅስቃሴ አሸንፎ ስልጣን ከያዘ አምስት አመት ሆነው። በነዚህ አመታት ውስጥ፣ኢትዮጵያ በብዙ ውጣ ውረድ  የተወሳሰበ የጭንቅ ጉዞ ላይ ትገኛለች። በአንድ በኩል አገሪቱን ወደ ዲሞክራሲያዊ ስርአት ሊያሸጋግሩ የሚችሉ አንዳንድ ለውጦች ተካሂደዋል። የፖለቲካ እስረኞች መፈታት፣  የፖለቲካ ስደተኞች ወደ  አገር መመለስ፣ ሃሳብን በነጻ የመግልጽ መብት እውቅና፣ መንግስት በተጨባጭ የወሰዳቸው እርምጃዎች ናቸው። ከነዚህ ከግለሰብ  መብቶች  ባሻገር፣ የዜጎች መሰረታዊ ሰብአዊ መብቶች ተከብረው በዲሞክራሲያዊ ስርአት ለመኖር እንድዲችሉ አንዳንድ መዋቅራዊ ለውጦችም ተደርገዋል። ከነዚህም መሀል የመሰብሰብና የመደራጀት መብት፣ የፕሪስ ነጻነት፣ በፖለቲካ የመደራጀት መብት ይገኙበታል። በተጨማሪም፣ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽንና የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ በነጻነት እንዲሰሩ የሚያስችላቸው መሰረት መጣሉ ወደ ዲሞክራሲ ስርአት ለመሸጋገር ትልቅ አስተውጽኦ የሚያደርጉ ናቸው።

በሌላ በኩል፣ የተገኙትን ድሎች ለመቀልበስ ብሄርተኛ የፖለቲካ ሃይሎች፣ ጽንፈኞችና ሽብርተኞች በመሳሪያ ትግል ጭምር ጸረ ዲሞክራሲና ጸረ ሰብአዊ መብት እንቅስቃሴያቸውን በስፋት ተያይዘውታል። ከነዚህም ሃይሎች መሀል በግንባር ቀደምትነት ይሚጠቀሰው ህወሃት ነው። ኢትዮጵያን 27 አመት በአምባ ገነንነት ከገዛ በሁውላ፣ መሪዎቹ እራሳቸው በፈጠሩት ህግ፣ በኢሃደግ ወስጥ በተፈጠረ ልዩነት ተሸነፉ ። በሁዋላም ጦርነት አወጁ። ዲሞክራሲን ተቃወሙ። የሰው ልጆችን ሰብአዊ መብት ገፈፉ። በተፈጠረው ጦርነት ሰላማዊ ሰዎች ተጨፈጨፉ፣  ሴቶች ተደፈሩ፣ ህጻናት ተሸማቀቁ፣ በሚሊዮን ይሚቆጠሩ ተፈናቀሉ።  የመሰረተ ልማት ተቋሞች ወደሙ። ይሄ የጸረ ዲሞክራሲና ጸረ ሰብአዊ መብት ሽብር በአገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች ሲካሄዱ ይታያል። በተለይም በኦሮሚያ ውስጥ  ጠንከር ባለ መልኩ ሽብርተኞች አካባቢውን እያመሱት ይገኛሉ።

የዚህን ግጭት መነሻ ለመረዳት በ1983 የህወሓት/ኢህአዴግን የስልጣን መያዝና የተከተለውን የፖለቲካ መስመር በአጭሩ መመርመር አስፈላጊ ነው። ኢህአዴግ፣ የአገዛዙ ዋና ገፅታ የሆነውን የብሄር ማንነትን፣ የሀገሪቱ የፖለቲካ ህይወት የማደራጃና የመምሪያ መርህ አድርጎ በማስቀመጥ ዛሬ ላለንበት ቀውስ በር ከፍቶአል።  የተባበሩት መንግስታት ድርጅት  የሰብአዊ መብት ድንጋጌን በመጣስ፣ በየክልሉ የሚገኙ አናሳ ብሄረሰቦች እንደ ሁለተኛ ዜጋ እንዲቆጠሩ፣ የብሄር የአምባ ገነንነት አስተሳሰብ እንዲዳብር፣ ሕዝብ እንዲፈናቀል፣ እንዲገደል፣ ብሔር ተኮር ግጭቶች እንዲስፋፉ፣ አስተዋጾ አድርጓል።

ጽንፈኝነትና ሽብርተኝነት ጸረ ዲሞክራሲ ናችው። ሽብርተኝነት ወንጀል ነው። የታጠቁም ሆኑ ያልታጠቁ ጽንፈኞች ለሰላም፣ ለዘላቂ ልማት ፣ ለሰብአዊ መብቶች መከበር፣  በህግ የበላይነት ለመተዳደር  የሚደርገውን የጋራ ጥረት  በመጻረር ቆመዋል። የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የፀጥታው ምክር ቤት በአክቶበር 2004 ባወጣው መግለጫ (ውሳኔ ቁጥር 1566) ሽብርተኝነትን እንድሚከተለው ይገልጽዋል። የሽብርተኝነት ድርጊቶች "በሰላማዊ ሰዎች ላይ የሚፈጸም  የወንጀል ድርጊት ፣ ለሞት ወይም ለከባድ የአካል ጉዳት የሚዳርግ፣ ሰላማዊ ሰዎችን የሚያግት ፣ ዓላማው በሕዝብ ወይም በቡድን ውስጥ ሁከትን፣ አለመረጋጋትን መቀስቀስ፣ ሕዝብን ማስፈራራት፣ መንግሥትን ወይም ዓለም አቀፍ ድርጅትን ለጥያቄያቸው መልስ እንዲስጥ ማስገደድ" ነው ይላል። በተጨማሪም፣ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ በዲሴምበር 2005 ሽብርን በሚመለከት ባሳለፈው ውሳኔ "በሕዝብ ላይ ሽብር ለመፍጠር የታቀዱ የወንጀል ድርጊቶች ምንም ዓይነት የፖለቲካ፣ የፍልስፍና፣ የርዕዮተ ዓለም፣ የዘር፣ የጎሣ፣ የኃይማኖት ወይም ሌሎች ምክንያቶችን እንደ መታገያ አላማ አድርገው ቢቀርቡ፣ የሽብርተኝነትን ድርጊት ከወንጀል ነጻ ስለማያደርገው ተቀባይነት የለውም" ይላል።

የዜጎች ሰብአዊ መብት መከበር በተግባር እንዲተረጎም፣ የዲሞክራሲ መሰረታዊ ህጎችን የእለት ተእለት መርሆ ለማድረግ፣ በህግ ለመተዳደርና ለመገዛት፣ የፖለቲካ ብዝሃነትን ያቀፈ ስርአት ለመገንባት፣ የኢትዮጵያ ዲሞክራቶች፣ ግለሰቦችም ሆኑ የፖለቲካ ድርጅቶች እንዲሁም የተለያዩ የህበረተሰቡ ክፍሎች  አቅማቸው በሚፈቅደው መሰረት፣ ድርሻቸውን መወጣት ይጠበቅባቸዋል። ይህም ማለት፣ በግልጽ የሽብርተኞችን ወንጀል አውግዘው፣ ለዲሞክራሲና ለሰብአዊ መብት መከበር ያላቸውን ወገንተኝነት በማሳየት፣ በህዝብ ጎን በመቆም፣ ዲሞክራሲ በተግባር እንዲተረጎም፣ ለዜጎች መብትና ህልውና በጋራ መታገል ይጠበቅባቸዋል።

**ድልድይ**፣  የጽንፈኝነት አደጋ በዛሬይቱ ኢትዮጵያ በሚል ርእስ ያዘጋጀው ኮንፈረንስ ዋና አላማም የጽንፈኝነት ፖለቲካን ከአለም አቀፍ የዲሞክራሲ፣ የሰብአዊ መብትና የህግ የበላይነት መርሆች አንጻር በመመርመር ግልጽ ውይይት  እንዲካሄድ ለማገዝ የታቀደ ነው።